# ይህንን ይወቁ

## 1. ፍቺ

መጀመሪያ ፍቺ ወደሚለው ከመግባታችን በፊት አማኝ የሚለው ቃል መፈታት አለበት። አማኝ ማለት ጌታ እየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለ ፣ በእርሱ የሚያምን ፣ ህይወቱን ሁሉ የሚመራው እርሱ መሆኑን በመረዳት በእርሱ አመራርና ትእዛዝ ስር የሚወድቅ ማለት ነው።ስለዚህ አማኝ ብሎ ስለ ፍቺ ማንሳት፣ ስለመለያየት ማንሳት የሚያስቸግር ይመስለኛል። ምክንያቱም በቀጥታ ከመንፈሳዊ ህይወት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው። በአማኞች ዘንድ ፍቺ ለምን በዛ ፣ ለሚለው ጥያቄ የጋብቻው መስራች የሆነውን ፣ እናምነዋለን የሚሉትን፣የሰጣቸውን ትዳር የሚመሩበትን የህይወት ቃል ወይንም የትዳራቸው ማእከል ጌታ እየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በመዘንጋት፣ ግዴለሽ በመሆን፣በእግዚአብሄርና በህዝቡ ፊት የገቡትን ቃል ኪዳን በመርሳት፣ ከአማኝነት የጎደለ የህይወት ምልልስ ውስጥ ስለሚገቡ፣ በመሃከላቸው የሚፈጠሩትን ግጭቶች ለመፍታት መንፈሳዊ መሆንን ስለሚጠይቅ፣ ይህ ደግሞ ያልተለማመዱት የህይወት መንገድ ስለሆነ ፣ ፍቺን እንደ አማራጭ በመውሰድ በአሁኑ ጊዜ ፍቺ በአማኞች ዘንድ እየበዛ መጥቷል።

ለፍቺ የሚያበቋቸው ምክንያቶች መሰረታቸው ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ከክርስቶስ ይልቅ አርስበርሳቸው ስለሚተያዩ ፣ ክርስቶስን ማእከል ሰለማያደርጉ በየእለቱ በሚያደርጉዋቸው እንቅስቃሴ ላይ ያተኩራሉ። መጽሃፍ ቅዱስ ስለባል መውደድና ስለ ሚስት መገዛት ከመናገሩ በፊት በኤፌሶን ምእራፍ 5:21 ላይ” ለእያንዳንዳችሁ

በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛቻሁ ሁኑ።" ይላል፤ ይህ ፍርሃት በቤታቸው ውስጥ ስለሌለ በእርስበርሳቸው የቴክኒክ አለመሟላት የተነሳ ወደ ፍቺ ሊያዘነብሉ ይችላሉ።

አለመግባባት፣ አለመከባበር፣አለመረዳዳት፣ አለመተሳሰብ፣አለመዋደድ፣በማድረግና ባለማድረግ ላይ ይተመሰረተ ግንኙነት፣ ሰለግብረስጋ ግንኙነት የመረዳት ልዩነት፣ እና ሌሎችም ምክንያቶች ቢኖሩ ዋናውና መሰረታዊው ምክንያት ግን በክርስቶስ ላይ የተመሰረተ ህይወት መኖርና አለመኖር ነው።

ይህንን ማስተካከል የሚቻለው በተፈጠረው የግጭት ምክንያት ላይ በማተኮር ሳይሆን በመጀመሪያ ህይወትን በመመርመርና መንፈሳዊ ህይወት እንዲታደስ ማድረግ ነው። የጋብቻ ወግ በእግዚአብሔር የመንግስት ስርአት ውስጥ ምን እንደሚመስል ማስረዳትና ለፍቺ የሚያበቃቸውን ግጭት መፍታትም እንደሚቻል በማሳሰብ ወደ ማስተዋላቸው በመመለስ አይናቸውን ወደ ቤቱ ራስ ወደ ክርስቶስ እንዲመልሱ ማድረግ ነው። ቤተክርስቲያን በየጊዜው የጋብቻ ትምህርቶችን በማዘጋጀት፣ የማማከር አገልግሎት ክፍል በመክፈት፣ የቤት ለቤት ጋብቻ ተኮር ህብረቶችን በማቋቋም፣ የጋብቻ አላማ በእግዚአብሔር ዘንድ ምን እንደሆነ በሚያስረዱ ፖስተሮች፣በራሪ ጽሁፎች፣ ስዕሎች በማዘጋጀት ምዕመኑን መቀስቀስ ማስተማርና መርዳት ይጠበቅባታል።

## 3. የፍቺ ምልክቶች

በትዳር ውስጥ ወደ ፍቺ ሊያመሩ የሚያስችሉ ምልክቶች አሉ፤ መፍትሄ ካልተሰጣቸው ፍቺው ሊከሰት ይችላል። ኣንዳንድ ምልክቶችን ለመግለጽ፤ አንደኛው የሌላኛው የበላይ ፣ አዛዥና ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ መታየት ሲጀምር፣ ለመወያየት ፈቃደኛ ሳይኮን ሲቀር፣ የቤቱ ሃላፊነት በአንዱ ላይ ብቻ ሲወድቅ፣ከቤት ይልቅ ወደ ውጪ የሚያዘነብል ልብ ሲከሰት፣ ፍቅር መስጠትንና መቀበልን አላመቻል፤የራስን አንጂ የሌላውን ወገን ጥቅም ለማስጠበቅ ሳይሞከር ሲቀር፤ገንዘብን በአግባቡ አለመጠቀም ወዘተ። እነዚህ ሁሉ የፍቺ ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ፤ በዋነኛ ደረጃ ግን አብሮ የእግዚአብሄርን ቃል አለማጥናትና አለመጸለይ፣ በቃሉ ውስጥ የተሰጣቸውን ድርሻ አለመወጣት ለሰይጣን ቀጥተኛ በር መክፈት ስለሚሆን ከምልክቶቹ ዋነኛና ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

# 4. ተግባቦት

የተግባቦትን ችግር ለመፍታት ባለትዳሮች እውነተኛና ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን አለባቸው። አንደኛው የሌላኛውን ሃስብ ለማዳመጥ፣ ጆሮዎቹን ፣ አይኑን ሁሉ ከፍቶ ያለምንም መዘናጋት፣ ያለምንም ጣልቃ ገብነት ለመስማት መዘጋጀት አለበት። ይቅርታ መጠየቅና ተራን ጠብቆ ሃሳብን መግለጽ በጣም አስፈላጊ ነው፤ በንግግር መሃል አላስፈላጊ የሆኑ ቃላቶችን መሰንዘርና አንደኛውን ክፍል ለመጉዳት ሆን ብሎ ከማሰብ መራቅና አንደበትን በመግዛት በጨው የተቀመመ አንዲሆን ጥረት ማድረግ፣ በጉዳዩ ላይ መነጋገር አንጂ እርስበርስ ለመጎዳዳትእንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ፣ ፍቅርን የተላበሰ አንዲሆን መጣር፣ አሁንም ለመግባባት ክርስቶስን ማእከል ያደረገ መሆን አለበት። የራስን የውሳኔ ሃሳብ ይዞ መቅረብ ሳይሆን

የሌላውንም ሃሳብ ለመቀበል መዘጋጀት ያስፈልጋል፤ እኔነት ወይንም እኔ ያልኩት ብቻ ከሚል ከራስ ወዳድነት ስሜት መውጣት ያስፈልጋል፤ በኣካል ምልክቶች በሚገለጹት ቃንቋዎች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ፣ ቁጣ ፣ንዴትና ጩኸት በምንም አይነት ሊከሰቱ አይገባም፡፡

# 5. ገንዘብ

ገንዘብን መውደድ የሃጢአት ሁሉ ስር እንደሆነ እንደዚሁም ለገንዘብና ለጌታ ለሁለቱም መገዛት እንደማይቻል መፅሐፍ  ቅዱስ ይነግረናል፤ ስለዚህ ገንዘብ አምላክ እስከ መሆን ይደርሳል ማለት ነው፤ገንዘብ አገልጋይ እንጂ መሪ አይደለም፣ እናዘዋለን እንጂ አያዘንም፤ በትዳር ውስጥም ስንጠቀምበት ባግባቡ ካልያዝነውና ካልተጠቀምንበት ወደ ፍቺ ሊመራን ይችላል፤ ምክንያቱም አንደኛው ቆጣቢ ሌላኛው አባካኝ ከሆኑ በሁለቱ መካከል መግባባት ይጠፋል፣ አንደኛው ከአቅሙ በላይ መኖር የሚፈልግ ሲሆንና ሌላኛው እንደ ዐቅማችን የሚል ከሆነ ግጭት ይፈጠራል፣ አንደኛው የእዳ ድፍረት ሲኖረው ሌላኛው እዳ ሲፈራ አለመግባባትና ግጭት ይፈጠራል፡፡ ስለዚህ ገንዘብን በአግባቡ አለመያዝና በጋራ በመነጋገር አለመጠቀም አለመግባባትን ስለሚፈጥር ፍቺ ሊከሰት ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ገንዘብን እንደ መገልገያ መሳሪያ አድርጎ በመቁጠር ገቢን ከወጪ ጋር በማጣጣም፣ በፕላንና በፕሮግራም በመኖር፣ በበጀት መንቀሳቀስ፣ በአቅም መቻዝና በይበልጥ ደግሞ ገንዘብን በአንድ የሂሳብ ቋት ውስጥ በማስገባት በጋራ በመጠቀም ፍቺን መከላከል ይቻላል፡፡

# 6. የወላጅ ጣልቃገብነት

መፅሐፍ ቅዱስ "ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ፣" ዘፍ 2:24 ብሎ ይነግረናል ይህ ማለት የራሱን የጋብቻ ህይወት ስለሚጀምር ፣ የራሱን ህይወት በራሱ አምራር ስለሚመራ፣ አሁን የሚመራ እንጂ የሚመራ ስላልሆነ፣ በአባቱና በእናቱ ስር ሆኖ ከሚያደርገው የተለየ ሀይወት ውስጥ ስለሚገባ፣ በኢኮኖሚው ረገድም ብቁ ስለሆነና ራሱን ማስተዳደርና መምራት ስልሚችል፣ የሚቀጥለውን አዲስ ትውልድ ለመምራት የበቃ ስለሆነ ኣብቱን እናቱን በመተው አዲሱን የሀይወት ጎዳና ይጀምራል ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ለወላጆቻቸው ያላቸውን ፍቅርና አከብሮት ይቀንሱ ወይንም ይተዉ ማልት አይደለም፤ አማቾች ይህንን በመረዳት እንደቀድሞው ያደርጉት ከነበረው አመራር  እራሳቸውን ፈጽመው ማውጣት አለባቸው፤ ትዳሩ የሁለቱ ተጋቢዎች እንጂ የእንሱ አይደለም፤ ምክር በተጠየቁ ጊዜ ብቻ ምክራቸውን የማካፈል እንጂ በጣልቃ ገብነት ተጽዕኖ በማምጣትና ልጅ ወደሆነው በማድላት ጫና በትዳሩ ላይ መፍጠር የለባቸውም፡፡ አነሱም በአንድ ወቅት እንደነዚህ ተጋቢዎች እንደነበሩ መርሳት የለባቸውም፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል የሚፈጠረው ግጭት የከፋ ይሆንና አስከ መፋታት ይደርሳሉ፡፡ ባለትዳሮችም ቤተሰቦቻቸውን በአግባቡ በመያዝና በትዳራቸው ውስጥ ምንም አይነት መብት እንደሌላቸው ማሳውቅ አለባቸው፤እርዳታን በሚመለከት በመመካከር ማድረግ እንጂ ወደ አንደኛው ወገን ማድላት በትዳሩ ላይ አደጋ ይፈጥራል፤ የትዳሩን ሚስጥር ለወላጆች በመግልጽና

አብሮ ትዳሩን መገምገም አግባብ አይደለም፤ እነዚህ ሁሉ ትዳሩን ሊያፈርሱ የሚችሉ መሳሪያዎች ስለሚሆኑ የአማቾች ጣልቃ ገብነትን ፈጽሞ በማስወገድ ትዳሩን ጤነኛ ማድረግ ያስፈልጋል።

# 7. ጊዜ

ምንም ይሁን ከትዳር ሻደኛ ጋር የግል ጊዜ ያስፈልጋል፤ የስራ ሰአትን መወስን፣ ከሁለት ሶስት ስራ ይልቅ ለቤተሰብ ቅድሚያ በመስጠት በኣንድ ስራ በሚገኝ ገቢ ለመኖር መሞከር፤ ጊዜ የሚያሳጣዉ ለገንዘብ ያለን የፍላጎት መጠን ከፍተኛ ስለሆነ ነው፤ ከኣቅማችን በላይ የገባንባቸውን እዳዎች ለመክፈል፣ እንዲህ አደርጋለሁ ወይንም አደርግላችኋለሁ እያልን የምንገባቸውን ቃል ኪዳኖች ለመፈጸም ስንል ጊዜያችንን በሙሉ ገንዘብ የሚያስገኝ ስራ ይወስድብናል።

እራስን ከአቅም በላይ በሆነ በቤተክርስቲያን አገልግሎት በመወጠር ፣ አራስን በራስ ጊዜ ለማሳጣት የምናደርጋቸው ድርጊቶች በሙሉ ከትዳር ሻደኛችን ጋር ጊዜ እንዳይኖረን ያደርጋል፤ ስለዚህ በመነጋገር ለሁሉም ጊዜ አለው በሚል መርህ በቀን በሳምንትና በወር ያሉትን ሰዓቶች በመከፋፈልና የጊዜ በጀት በማውጣት በፕሮግራም ልንጠቀም እንችላለን፤ ላወጣነው ፕሮግራም ደግሞ ፈጽሞ ታማኝ መሆን አስፈላጊ ነው።

# 8. ሶሻል ሚዲያ

የሶሻል ሚዲያ በመሰረቱ ጎጂ አይደለም፤ ከአጠቃቀም ጉድለት የተነሳ ግን ምነው እንዲህ አይነት ጉድ ባልተፈጠረ በማለት

ቴክኖሎጂውን እስከ መርገም ያስደርሳል፡፡ ከትዳር ጓደኛ ጋር ከመጫወትና ከመነጋገር ይልቅ በፌስ ቡክና በዩትዩብ ላይ ጊዜን ማጥፋት በሁለቱ መካከል ያለውን ተግባቦት ያደፈርሳል፣ መንፈሳዊ ህይወትን ይበላል፣ለሱሰኝነት የዳርጋል፤ ለዲፕረሽን ይዳርጋል፣ብቸኛ ያደርጋል፣ ከባል ከሚስት ከልጆች ይለያል፤ በቤት ውስጥ መሰራት የሚገባቸውን ስራዎች ጊዜ ይወስዳል፡ ወሬኛ ወሬ ፈላጊ ያደርጋል፤ በስልክ ከመጠን በላይ ማውራትና የተከታተሉ ጥሪዎችን መቀበልና በተደጋጋሚ መደወል ለትዳር ጓደኛችን ልንሰጠው የሚገባውን ጊዜ ይበላል፤ በስልክ የሚደረግ መንፈሳዊ ኮንፍራንስ ቢቻል ባይደረግ ይመረጣል፡፡ ጊዜን ከመብላቱ በላይ የሚሰጡት ትምህርቶች ጥራትና ይዘት፣ የኣስተማሪዎቹ ወይንም የሰባኪዎቹ ማንነትና የማስተማር ብቃት የተረጋገጠ ካለመሆኑ የተነሳ ለስህተት ትምህርት በቀላሉ ለመዳረግ መንገድ ሊሆን ይችላል፤ከዚህ መላቀቅ የማይቻል ከሆነ ጊዜና መጠን ቢኖረው መልካም ነው፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱ የትዳር ጓደኛሞች መስማማትና መቀባበል በመነጋገርና እራስን በጊዜ ውስጥ በመወሰን ሚዛናዊ ማድረግ ይቻላል፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ መንፈሳዊ ህይወትን የሚበላ መስሎ ከታየ እርግፍ አርጎ መተው ብልህነትና ጥበበኛነት ነው፡፡